የሰ/መ/ቁጥር-

--235470

ቀን- ግንቦት 30 ቀን 2015 ዓ.ም

**ዳኞች:-** ብርሃኑ አመነዉ

ረታ ቶሎሳ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ኑረዲን ከድር

**አመልካች:-** መጋቢ ስርዓት ዮሴፍ አብተዉ- ቀረቡ

**ተጠሪዎች:-** 1. የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት

2. የቦሌ ደብረሰላም መድኃኔዓለም መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ካቴድራል አስተዳደር ጽ/ቤት አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የደመወዝ ጭማሪና የአበል ክፍያን የተመለከተ የሥራ ክርክር ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ፣ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ ሲሆኑ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 87451 ሰኔ 06 ቀን 2014 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 293959 ነሐሴ 25 ቀን 2014 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

አመልካች የካቲት 06 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- አመልካች በ2ኛ ተጠሪ ካቴድራል በጠቅላላ አገልግሎት የስራ መደብ ተቀጥረዉ በወር ብር 12,354 እየተከፈላቸዉ ሲሠሩ የቆዩ ሲሆን የ2ኛ ተጠሪ ጽ/ቤት ከጥቅምት 11 ቀን 2014 ዓ.ም በቁጥር 166/ለ9/2014 ለ1ኛ ተጠሪ በጻፈዉ ደብዳቤ ለ4 የካቴድሉ አስተዳደር ሠራተኞች ቀደም ሲል በ2013 ዓ.ም የደመወዝ ስኬሉ ገድቧቸዉ ስለነበረ የተሻሻለዉ የደመወዝ ስኬል መሠረት የታለፈባቸዉ ደመወዝ እንዲጨመርላቸዉ በማለት 1ኛ ተጠሪን ጠይቆ በተሰጠዉ ምላሽ ለእያንዳንዳቸዉ ብር 3,824 ደመወዛቸዉ ላይ እንዲጨመር ፈቅዷል፡፡ በዚሁ መሠረት 2ኛ ተጠሪ ለተጠቀሱት ሠራተኞች ከጥቅምት 01 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የደመወዝ ጭማሪዉን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ አመልካች ከተጠቀሱት ሠራተኞች ጋር በደመወዝም ደረጃ ሆነ በሙያ ተመሳሳይ የሥራ መደብ ላይ የነበሩ በመሆናቸዉ በተሻሻለዉ የደመወዝ ስኬል መሠረት ብር 3,824 እንዲጨመርላቸዉ እንዲሁም ቀደም ሲል ያልተከፈላቸዉ የትራንስፖርት እና የጥቅማጥቅም አበል እንዲከፈላቸዉ 1ኛ ተጠሪን ቢጠይቁም ምላሽ አለማግኘታቸዉን፣ በተጨማሪም ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የፓትሪያርኩ ልዩ ጽ/ቤት ታሕሳስ 04 ቀን 2012 ዓ.ም 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች ጥቅማጥቅምና የትራንስፖርት አበል በየወሩ ብር 4,000 እንዲከፍል ትዕዛዝ ቢያስተላልፍም ብር 2,500 ብቻ በመክፈል ብር 1,500 ለመክፈል ፍቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለሆነም የደመወዝ ጭማሪዉ በወር ብር 3,824 ከጥቅምት 01 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ታስቦ እንዲሁም የጥቅማጥቅም እና የትራንስፖርት ልዩነት ብር 1,500 ከታሕሳስ 04 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ታስቦ እንዲከፈላቸዉ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

ቀን- ግንቦት 30 ቀን 2015 ዓ.ም

1ኛ ተጠሪ ለቀረበበት ክስ የካቲት 21 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የመከላከያ መልስ ይዘት፡- 1ኛ ተጠሪ ለይቶ የደመወዝ ጭማሪ አለማድረጉን፤ ጭማሪ ያጸድቃል እንጂ በቀጥታ የማይጨምር በመሆኑ ክሱ የክስ ምክንያት የለዉም ተብሎ ዉድቅ እንዲደረግ፡፡ ለቦታዉ የተፈቀደ አበል ሲከፈላቸዉ የቆዬ በመሆኑ ዳኝነት የሚጠይቁበት ካለመሆኑም በላይ በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ አመልካች የ2ኛ ተጠሪ ጽ/ቤት የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኛ መሆናቸዉን፤ ለሌሎች የሥራ ኃላፊዎች የእስኬል ማስተካከያ ሲደረግ ተከልክያለሁ በማለት የጠየቁት ጥያቄን በተመለከተ ቤተክርስቲያኒቱ ከምትተዳደርበት ቃለ አዋዲ ሕገ-ደንብ አንቀጽ 16 ስር ከተዘረዘሩት የሥራ ክፍሎች ዉስጥ የጠቅላላ አገልግሎት የስራ መደብ የሌለና ተራ የስራ መደብ በመሆኑ ከሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ጋር ደረጃቸዉ እኩል ባለመሆኑ ለሌሎች የተጨመረዉ ይጨመርልኝ የሚለዉ ተቀባይነት የለዉም፡፡ የደመወዝ ጭማሪ እንደማበረታቻ የሚሰጠዉ የአገልግሎቱ መጠንና የስራ አፈጻጸሙ ታይቶና ተገምግሞ ብቁ ሆኖ ሲገኝ ነዉ፡፡ ለካቴድራሉ ሠራተኞች የእስኬል ማስተካከያ ጭማሪ የተደረገላቸዉ ቀደም ሲል ለጠቅላላ ሠራተኞች የደመወዝ ጭማሪ ሲደረግ እስኬል ገድቧቸዉ የቆዩ በመሆናቸዉ የሚያከናዉኑት የሥራ ተግባር ተገምግሞ የእስኬል ደረጃዉ ሲሻሻል በካቴድራሉ ሰበካ ጉባኤ በኩል ታይቶ ስለታመነበት ለ1ኛ ተጠሪ ጥያቄዉ ቀርቦ ለካቴድራሉ ዋና አስተዳዳሪ፣ ዋና ፀሐፊ፣ ሒሳብ ሹም እና ቁጥጥር ሠራተኞች ደመወዝ ስኬሉ ገድቧቸዉ የቆየዉ ተሻሽሎ እንዲጨመርላቸዉ የጸደቀ በመሆኑ የአመልካች ጥያቄ ተገቢነት የለዉም፡፡

ጥቅማጥቅምና የትራንስፖርት አበል በየወሩ ብር 4,000 እንዲከፈላቸዉ የፓትሪያርኩ ጽ/ቤት የወሰነበት አግባብ የለም፤ ደብዳቤዉ እንደሁኔታዉ ዳኝነት ይታይላቸዉ በሚል ተሰጠ ማሳሰቢያ ነዉ፡፡ ለቦታዉ የሚገባዉ አበል ለአመልካች እየተከፈላቸዉ በመሆኑ ጥያቄዉ ተገቢነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

2ኛ ተጠሪ የሚመለከተዉ የካቴድራል ጽ/ቤት በመሆኑ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ትዕዛዝ የተሰጠ ቢሆንም ቀርቦ ያልተከራከረ በመሆኑ የመከራከር መብቱ የታለፈ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ፣ ምስክሮችን ሰምቶ፣ አጣርቶና መርምሮ፡- ለአመልካች ከጥር 01 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ብር 2,466 ጭማሪ ተደርጎላቸዉ ብር 12,354 ጸድቆ ሲከፋላቸዉ የነበረ በመሆኑ በ2013 ዓ.ም የቀረባቸዉ ጭማሪ አለመኖሩንና በ2014 ዓ.ም ለተጠሪ ሠራተኞች ጭማሪ ሲደረግ ከመጋቢት 01 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ለአመልካች ብር 1,783 የተጨመረላቸዉ መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች ላይ የተፈጸመ አድሎ ባለመኖሩ ጥያቄዉ ተገቢነት የለዉም እንዲሁም ከፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት ጥቅማጥቅም እና የትራንስፖርት አበል ብር 4,000 እንዲከፈላቸዉ ትዕዛዝ ቢሰጥም ሲከፈላቸዉ የቆየዉ ብር 2,500 ብቻ በመሆኑ ቀሪዉ ብር 1,500 ታስቦ እንዲከፈላቸዉ የተጠየቀዉን በተመለከተ አመልካች የቅጥር ዉል ያለዉ ከተጠሪ ጋር በመሆኑና የፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት ከአመልካች ጋር ቀጥታ የዉል ግንኙነት የሌለዉ በመሆኑ የጽ/ቤቱን ትዕዛዝ ተጠሪ ለመፈጸም ባይፈቅድ በትዕዛዙ መሠረት እንዲፈጽም ፍርድ ቤት የሚወስንበት አግባብ የለም በማለት የአመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካች ሰበር አቤቱታ ይዘት፡- አመልካች ከሥራ ባልደረቦቹ ተለይቶ ጭማሪ ያለአግባብ የተከለከለዉ ከጥቅምት ወር 2014 ዓ.ም ጀምሮ በተደረገዉ ጭማሪ ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤቱ አመልካች ካቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ዉጭ ወጥቶ በ2013 ዓ.ም የደመወዝ ጭማሪ ተጠቃሚ ነበሩ ወይስ አልነበሩም የሚል ጭብጥ በመያዝና ተጠሪ በ2013 ዓ.ም

እንደሌላዉ ሠራተኛ ተጨምሮላቸዋል የሚል መልስ ስላቀረበ ብቻ በ2013 ዓ.ም አመልካች የቀረበባቸዉ ጭማሪ የለም በማለት ማለፉም ሆነ አመልካች እንደሌሎች ሠራተኞች ከመጋቢት 1 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ብር 1,783 ተጨምሮላቸዋል በማለት ስለጥቅምት ወር 2014 ዓ.ም የደመወዝ ጭማሪ ምንም ሳይል የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ በመግፋት ማለፉ ስህተት ነዉ፡፡ ተጠሪ ተጠይቆ ስለጥቅምት ወር 2014 ዓ.ም የደመወዝ ጭማሪ ለሌሎች ሠራተኞች በልዩነት ላደረገዉ የደመወዝ ጭማሪ እንደምክንያት ያስቀመጠዉ በተለያዬ የጭማሬ ዓመታት እየተቆረጠባቸዉ ስለቆዬ ነዉ የሚል ምክንያት ሆኖ እያለ ፍ/ቤቱ በመጋቢት ወር 2014 ዓ.ም የደመወዝ ጭማሪ ላይ ተመስርቶ መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ አመልካች የደመወዝ ጭማሪዉ ከተደረገላቸዉ ሠራተኞች በብሔር ወይም በፖለቲካ አመለካከት የተለዩ ከመሆናቸዉ አንጻር በአድሎ የተደረገባቸዉ መሆኑን የሚያሳየዉ ለገንዘብ ያዥ ሠራተኛ ለሆኑት ለአባ ወ/ዮሐንስ እንዳለ በልዩነት የደመወዝ ጭማሬዉን ያደረገበትን በቂና አሳማኝ ምክንያት አልሰጠም፡፡ በተጨማሪም የጥቅማጥቅምና የትራንስፖርት አበልን አስመልክቶ የፓርትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት የሰጠዉን ትዕዛዝ 1ኛ ተጠሪ አለመፈጸሙና ጽ/ቤቱም የበላይ መሆኑን አረጋግጦ ባለበት ትዕዛዙ የሚፈጸመዉ የበታች አካል ሲፈቅድ ብቻ የሚፈጸም እንደሆነ አድርጎ የስር ፍ/ቤት ማስቀመጡ ተገቢ አይደለም፡፡ በመሆኑም በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ መሠረት እንዲወሰንላቸዉ ጠይቀዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ከሌሎች በሙያ ደረጃ እና በልምድ እኩል ደረጃ ካላቸዉ ሠረታኞች ጋር የደመወዝ ጭማሪ ሳይደረግላቸዉ የታለፈበትን አግባብ ለማጣራት ሲባል መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ነዉ፡፡

ተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸዉ መልስ ባለመቅረባቸዉ በጽሁፍ መልስ የማቅረብ መብታቸዉ የካቲት 08 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ ታፎባቸዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሹ ጭብጦች የስር ፍ/ቤት፡-

1. አመልካች ታለፈብኝ የሚሉት ጥቅምት ወር 2014 ዓ.ም ለሌሎች ሠራተኞች የተደረገዉ የደመወዝ ጭማሪ ሆኖ እያለ በ2013 ዓ.ም እና በመጋቢት 214 ዓ.ም በተደረገዉ የደመወዝ ጭማሪ ላይ ተመስርቶ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ ማድረጉ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? እንዲሁም
2. ጥቅማጥቅምና የትራንስፖርት አበልን አስመልክቶ የተጠሪዎች የበላይ አካል የሆነዉ የፓትርያርኩ ልዩ ጽ/ቤት ለአመልካች በየወሩ ብር 4,000 እንዲከፈላቸዉ ትዕዛዝ መስጠቱ እና ሲከፈላቸዉ የነበረዉ ብር 2,500 ብቻ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ቀሪዉ ብር 1,500 በአስተዳደራዊ መልኩ ካልሆነ በቀር በፍርድ ሊወሰን አይችልም በማለት የተሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚሉት ናቸዉ፡፡

**የመጀመሪያዉን ጭብጥ በተመለከተ፡-** በመሠረቱ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 14(1/4) በብሔር፣ በጾታ፣ በሀይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ በአካል ጉዳት እና በሌላም ሁኔታ በሠራተኞች መካከል በአሠሪዉ ወይም በሥራ መሪ የአድሎ ተግባር መፈጸም ሕገ-ወጥ ተግባር መሆኑ በማያሻማ ሁኔታ ተደነገጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለዉ በደመወዝና በጥቅማጥቅም ጭማሬም ሆነ በሌላ ተግባር አሠሪዉ ወይም የሥራ መሪዉ ከላይ ከተገለጹት ሁኔታዎች መካከል በአንዱ ላይ ተመስርቶ በሠራተኞች መካከል አድሎ ሊፈጽም የማይችል

ቀን- ግንቦት 30 ቀን 2015 ዓ.ም

መሆኑን ሲሆን ሆኖም የደመወዝና የጥቅማጥቅም አጨማመር ሥርዓት ዘርግቶ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ሠራተኞች መስፈርርቱን ካላሟሉ ሠራተኞች የተለዬ ወይም የተሻለ ክፍያ የሚከፈልበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉ በሠራተኞች መካከል አድሎ ፈጸመ የሚያስብል ካለመሆኑም በላይ ተግባሩ ሕገ-ወጥ ነዉ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች አጥብቀዉ የሚከራከሩት የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኛ ሆነዉ ከሌሎች ማለትም ከካቴድራሉ ዋና አስተዳዳሪ፣ ዋና ፀሐፊ፣ ሒሳብ ሹም እና ቁጥጥር ሠራተኞች ጋር እኩል ብር 12,354 ደመወዝ ሲከፈላቸዉ ቆይቶ ጥቅምት ወር 2014 ዓ.ም የደመወዝ እስኬል ማስተካከያ ተደርጓል በሚል ለእያንዳንዳቸዉ ብር 3,824 ሲጨመር ያለአግባብ ለአመልካች ሳይጨመር ቀርቷል በሚል ነዉ፡፡ ፍሬ ነገርን አጣርተዉና ማስረጃ መዝነዉ ለማረጋገጥ ስልጣን የተሰጣቸዉ የስር ፍ/ቤቶች እንዳረጋገጡት ጥቅምት ወር 2014 ዓ.ም የደመወዝ ጭማሪ የተደረገላቸዉ ሠራተኞች አስቀድሞ በ2013 ዓ.ም እና ከዚያ በፊት በተደረጉት የደመወዝ ጭማሪዎች መነሻነት የደመወዝ እስኬሉ ጣሪያ ላይ በመደረሳቸዉ እስኬሉ ገድቧቸዉ የነበሩ መሆናቸዉን፤ አመልካች በጥር ወር 2013 ዓ.ም በካቴድራሉ ጸድቆ ተግባራዊ በተደረገዉ የደመወዝ ስኬል ሰንጠረዥ ተራ ቁጥር 7 ስር ብር 2,466 ተጨምሮላቸዉ ብር 12,354 ሲከፈላቸዉ የነበረ መሆኑና የደመወዝ እስኬሉ በወቅቱ ያልገደባቸዉ በመሆኑ በጥቅምት ወር 2014 ዓ.ም በደመወዝ እስኬል ማስተካከያ ምክንያት ሊጨመርላቸዉ የሚችል የደመወዝ ጭማሬ ባለመኖሩ አልተጨመረላቸዉም በሚል ነዉ፡፡ ከዚህ ጊዜ በኃላም ቢሆን ከመጋቢት 01 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ በተደረገ የደመወዝ ጭማሪ ብር 1,783 የተጨመረላቸዉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ ጥቅምት ወር 2014 ዓ.ም የተደረገዉ መደበኛ የደመወዝ ጭማሪ ሳይሆን የደመወዝ እስኬል ማስተካከያ ሲሆን በማስተካከያዉ መሠረት ቀድሞ የነበረዉ እስኬል ገድቧቸዉ ለነበሩ ሠራተኞች ማስተካከያ መደረጉ እና የአመልካች ደመወዝ በወቅቱ በእስኬሉ ያልተደገበ በመሆኑ ተመሳሳይ ክፍያ ይከፈላቸዉ ከነበሩ ሠራተኞች አንጻር ማስተካከያ አለመደረጉ በበቂ ምክንያት ላይ የተመሠረተ እንጂ በማንኛዉም ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የተደረገ አድሎ አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት ለደረሰበት መደምደሚያ በመነሻነት የጥር ወር 2013 ዓ.ም እና የመጋቢት ወር 2014 ዓ.ም መደበኛ የደመወዝ ጭማሪዎችን መጥቀሱ የጥቅምት ወር 2014 ዓ.ም የደመወዝ እስኬል ማስተካከያን አልተመለከተዉም የሚያስብል አይደለም፡፡

ከላይ ከተገለጸዉ በተጨማሪ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ ላይ ተጠሪ የሌሎችን ጭማሪ ተገቢነት ሲገልጽ ገንዘብ ያዥ ለሆኑት ለአባ ወ/ዮሐንስ እንዳለ ማስተካከያ የተደረገበትን ምክንያት አለመግለጹ በአመልካች ብሔር ወይም ፖለቲካ አመለካከት ላይ ተመስርቶ 1ኛ ተጠሪ አድሎ ያደረገ መሆኑን ያሳያል በማለት ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ የሌሎችን ምክንያት ገልጾ የአንዱን ሠራተኛ ጭማሪ ምክንያት አለመግለጹ ብቻዉን አድሎ ማድረጉን የሚያረጋግጥ ካለመሆኑም በላይ ያለአግባብ ተጨምሮ ከሆነም የዚሁ ሠራተኛ ደመወዝ ተቀንሶ ከሚስተካከል በቀር የአመልካችን ደመወዝ ያለአግባብ ለመጨመር ምክንያት አይሆንም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የአመልካች የደመወዝ ጭማሪ የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ ማድረጉ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት አልተገኘም፡፡

**ሁለተኛዉ ጭብጥ**፡- ጥቅማጥቀምና የትራንስፖርት አበልን አስመልክቶ የተጠሪዎች የበላይ አካል የሆነዉ የፓትርያርኩ ልዩ ጽ/ቤት ለአመልካች በየወሩ ብር 4,000 እንዲከፈላቸዉ ትዕዛዝ መስጠቱ እና ሲከፈላቸዉ የነበረዉ ብር 2,500 ብቻ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ቀሪዉ ብር 1,500 በአስተዳደራዊ መልኩ ካልሆነ በቀር በፍርድ ሊወሰን አይችልም በማለት የተሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ሲሆን በርግጥ የፓትርያርኩ ልዩ ጽ/ቤት የተጠሪዎች የበላይ አካል ሊሆን የሚችል ቢሆንም ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ያላቸዉ የሥራ ግንኙነት የሚመራዉ በመካከላቸዉ

ባለዉ የስራ ዉል በመሆኑ፤ ተጠሪዎችም በራሳቸዉ አሠሪነት ክስ የቀረበባቸዉ በመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ሆነ በሥራ ዉላቸዉ መሠረት ከሚገደዱ በቀር በአስተዳደር ረገድ የበላይ የሆነዉ ጽ/ቤት ትዕዛዝ ስላስተላለፈ ብቻ የጥቅማጥቅምና የትራንስፖርት ጭማሪዉን ተገድደዉ በፍርድ እንዲጨምሩ የሚወሰንበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም የጽ/ቤቱ ትዕዛዝ በተጠሪዎች ካልተፈጸመ ባላቸዉ አሠራር በአስተዳደር ረገድ እንዲፈጽሙ ከሚደረግ በቀር ተጠሪዎች በፍርድ ተገድደዉ ጭማሪዉን እንዲያደርጉ የሚወሰንበት አግባብ ባለመኖሩ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች የደረሰቡት ድምዳሜ የሚነቀፍበት አግባብ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 87451 ሰኔ 06 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 293959 ነሐሴ 25 ቀን 2014 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/በ